## ወንጌልና በወንጌል ማመን ሞኝነት ነውን?

**በጌታ ኢየሱስ አማካይነት የተገኘው የአዲስ ኪዳን ወንጌል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ መጠሪያዎች ሲጠራ ይታያል፤** እነዚህም፡ -

- የእግዚአብሔር ወንጌል፣ ማር 1፡14፣ ሉቃ 4፡43፤
- የእግዚአብሔር ልጅ የክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል፣ ማር 1፡1፣ ሐሥ 8፡35፣ 11፡20
- የእግዚአብሔር መንግስት ወንጌል፣ ማቴ 24፡14
- የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል፣ ሐሥ 20፡24፣
- የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን፤ 2ቆሮ 4፡4

1ቆሮ 1፡20-21፣ "በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗል፤"
1ቆሮ 1፡25 "ምክንያቱም ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፤ ከሰውም ብርታት ይልቅ የእግዚአብሔር ድካም ይበረታል።"

ከእነዚህ ጥቅሶች አንጻር ሲታይ የወንጌል ስብከት ቂላቂሎች የሚሰብኩት፣ ሞኞች አድማጮችም ዝም ብለው በሞኝነት የሚቀበሉትና በሞኝነት የሚኖሩት ነው ማለቱ ይሆን? እግዚአብሔርስ በሞኞች ደስ የሚሰኝ ሞኝ ነው ማለቱ ይሆን?

### ወንጌል ለአይሁዳዊያን መሰናክል ሆነ

የብሉይ ኪዳን ሕግጋት የሚያውቁት የእስራኤላውያን መሪዎችና የሕግ መጻህፍት አዋቂዎች/ተንታኞች (ጸሐፍት፣ ፈሪሳዊያን፣ ሰዱቃውያን) የብሉይ ኪዳን ሕግ መጻህፍት ስብከትን ይደግፉና ይሰብኩም የነበሩ ቢሆንም ግን ራሳቸው ሕጉን አይጠብቁትም ነበር፤ ዮሐ 7፡19፡፡ የመሲሁ መምጣት ተስፋ አድርገው ይጠባበቁ ነበር፡፡ በመጣ ጊዜ ግን አመጣጡ እነርሱ በጠበቁት ሁኔታና ዓላማ ስላልነበረ አልተቀበሉትም፤ እንዲያውም ተቃወሙት፡፡ ወንጌል ለነርሱ መሰናክል ሆኖባቸዋል፡፡ ከዚያም አልፎ በአሁኑ ትውልድ ዘመን ያሉ የአይሁድ የብሉይ ኪዳን ሕግና ስርዓት ተከታዮች ሳይቀር አሁንም ቢሆን መሲሁ እንደመጣ አያምኑም፣ ገና ወደፊት ይመጣል/ይወለዳል ብለው ይጠባበቃሉ፡፡

### በምዕራፉ የዚህ ዓለም ጥበበኞች/ አዋቂዎች የሚላቸው፡-

በተለይ የግሪክ ጥበበኞች በአጠቃላይ የአህዛብ ፈላስፎች፣ በሰው መስፈርት ጥበበኞች ናቸው ተብዬዎች፣ የወቅቱ የዓለም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ችግሮች መፍትሂ አለን ብለው የሚያስቡ ስለነበሩ የወንጌልን ስብከት እንደ ሞኝነት ቆጥረውታል፡፡ የአሁኑ የግሪክ ዋና ከተማ አቴንስ በከተማይቱ ትመለክ በነበረችው ጣዖት ስም አቴና ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚያች ከተማ ወንጌልን ስለ ሰበከ አንዳንዶቹ ፈላስፎች፣ ቁም ነገር ይናገራል ብለው ስላላሉ "ይህ ለፍላፊ ምን ለማለት ይፈልጋል"? ይሉት ነበር፡፡

ወንጌል ሞኝነት ነው ብለው ያሉበት ምክንያትም በራሳቸው ጥበብና ፍልስፍና እግዚአብሔርንና አሰራሩን መርምረው ሊደርሱበት ስላልቻሉ ነበር፡፡ እንደዚህ ዓይነት

ሰዎችን ግን እግዚአብሔር ሞኞች ይላቸዋል፡፡ (ሮሜ 1፡18፣ 21-23, 1ቆሮ 2፡14፤ 3፡18-20፤) የወንጌሉ ቃል ሞኝነት ነው ያሉት የጽድቅን ሥራ የሚንቁትና ኃጢአት የሚወዱትን፣ ልባቸው በተለያየ ኃጢአት የተሞሉት፣ በራሳቸው ሰው ሰራሽ ጥበብ ተማምነው አዋቂዎች ነን የሚሉትን፣ በተለያዩ እንስሳትና ፍጥረታት ምስል ጣዖታት ቀርጸው በራሳቸው ላይ አምላክ አድርገው በመሸም የሚያመልኩት፣ ኅሊናቸው የደነዘዘባቸው ሰዎች ነበሩ፡፡

ስለዚህ ወንጌል ሞኝነት ነው የተባለው ራሳቸው አዋቂዎች የሆኑ በሚመስላቸው ነገር ግን ስለ መንፈሳዊ ነገር ትክክለኛ መረዳት በሌላቸው ሰዎች ዘንድ እንጂ በእግዚአብሔርና የወንጌል ዕውነት በሚረዱ ሰዎች ዘንድ አይደለም፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስም ወንጌልን "የስብከት ሞኝነት" ብሎ ሲል ዘይቤያዊ (ቀጥተኛያልሆነ) አነጋገር ተጠቀመ እንጂ ወንጌል በእርግጥ ሞኝነት ነው ማለቱ እንዳልሆነ በቀጣይ ምዕራፎች ያስተማረው ትምህርት ያረጋግጣል፡፡ (ምሳሌ 1ቆሮ 2፡6-7)

የዚህ ዓለም ጥበበኞች ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ክርስቲያኖችም ከላይ የተጠቀሱት ስለ ሞኝነት የሚናገሩ ጥቅሶች በመያዝና አላግባብ በመተርጎም "የወንጌልን ቃል መከተል በሞኝነት ነው" የሚሉ አሁንም ስላሉ ስለ ወንጌሉ ቃል ትክክለኛ ምንነት ላልተረዱት ማስረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

**መጽሀፍ ቅዱስ ጥበብን በሁለት አብይ ክፍሎች ከፍሎ ያሳየናል፡-**

1. ከምድር የሆነ ፍልስፍና የሚገኝ፣ ከስጋዊ ሰውና ከአጋንንት የሚመጣ፣ በሰው ሰራሽ ወግ የተመሰረተ፣ ክፋትና ኃጢአት የሞላው- የረከሰ ጥበብ ነው፤ (ያዕ 3፡13-15)
2. ከእግዚአብሔር የሆነ ንጹኅ ጥበብ፣ መንፈሳዊ እውነትና መልካም ፍሬ ተትረፍርፎ በዝቶ የሚታይበት የጽድቅ ሕይወትን፣ እግዚአብሔርን መፍራትን፣ መዳን የሚገኝበት የወንጌል ቃልን፣ ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚያደርሰው እምነትና ፍቅርን ነው፡፡ (ያዕ 3፡17)

የዓለም የምርምርና የፍልስፍና ትምህርት እንዲሁም የእስራኤላዊያኑ ታምራዊ ምልክቶች መፈለግ መጥፎ ላይሆን ይችላል፡፡ የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል የሆነው ወንጌል መናቃቸው ግን መሳት ነው፡፡ እግዚአብሔርም ለሰው ዘር መዳን የሰጠው እነርሱ የፈለጉትን ሳይሆን ያልጠበቁትን የተሰቀለውን ክርስቶስን ነው፡፡

**ወንጌል በእግዚአብሔርና የሚያስተውል አዕምሮ ባላቸው ሰዎች እይታ ሞኘነት ሳይሆን፣ እጅግ የከበረ ነገር መሆኑን የሚያሳዩ የቃሉ ክፍሎች ከዚህ በታች ሰፍረዋል፡-**

*1 ቆሮ 1፥18፣ “የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።”*

*1 ቆሮ 1፥24፣ “እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን፣ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው።”*

*1ቆሮ 1፡30፣ "ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኖአል።"*

*2 ቆሮ 4፡3፣4፣6፣ "ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ፣ የተከደነው ለሚጠፉት ነው። [4] የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል። ... 6 "በክርስቶስ ፊት እግዚአብሔር **የክብሩን ዕውቀት ብርሃን** ይሰጠን ዘንድ፣ **"በጨለማ ብርሃን ይብራ" ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በልባችን አብርቶአልና።"***

ወንጌል ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያደርስ/የሚመራ ከእግዚአብሔር የሆነ ጥበብና ብርሃን መሆኑን ከፍ ብሎ የሰፈሩት ጥቅሶች ያሳያሉ፡፡

**"ብርሃን" የተለያዩ መንፈሳዊ ነገሮች በምሳሌነት/በአመልካችነት የሚነገሩበት (ሲምቦላይዝ የሚያደርግ) ነው፡፡ እነዚህም፡-**

**ሀ. ሀሰት ያልተቀላቀለበት የእግዚአብሔር/መንፈሳዊ የጠራ እውነት ቃልና የሚያስገኘው በረከት፡፡** የወንጌል እውነት የእግዚአብሔርን ሕግ የማያውቁ በነበሩ ብዙ አህዛብና አነስ ያሉ የእስራኤላውን ድብልቅ ህዝብ በሚኖርባት ገሊላ፣ እንዲሁም በተለያዩ አገራት አህዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ብርሃን በመቀበል ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ሲድኑ፣ "በጨለማ የሚኖር ህዝብ ታላቅ ብርሃን አየ"፣ ተብሎ በኢሳያስ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ፡፡ ኢሳ 9፡2

**ለ. የጽድቅ ስራ፤ ቅድስና፣ እንከን የሌለበት ፍጹም ንጽህና፤ ኃጢአት አልባ መልካምነት፤ ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው፡፡** ባላመኑት መካከል መልካም ተግባር በመፈጸም መልካም ምሰሌ መሆንን የሚያመለክት ነው፡፡፡ ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ሲል የተናገረው ለዚህ ነው፡፡

ዮሐ 9፥5፣ "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ።" –

ማቴ 5፡14-16፣ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም፤ [15] ሰዎችም መብራት አብርተው ከዕንቅብ ሥር አያስቀምጡትም፤ በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲያበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡታል እንጂ። [16] እንደዚሁም ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ።"

**ሐ. ተደብቆ/ተሰውሮ የኖረ ምስጢራዊ ነገርን በአደባባይ ገሀድ ሲደረግ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ለረጅም ዘመናት ምስጢር ሆነው የቆዩና በወንጌል አማካይነት እግዚአብሔር ግልጽ ያደረጋቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ ለመጥቀስ ያህል፡ -**

1 ቆሮ 2፡7-8፣ ነገር ግን (ወንጌል) ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ምስጢር ጥበብ ነው፤ ይህም ጥበብ እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ለክብራችን አስቀድሞ የወሰነው ነው። [8]

ከዚህ ዓለም ገዦች አንዳቸውም ይህን ጥበብ አልተረዱትም፤ ቢረዱትማ ኖሮ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉት ነበር።

ቆላ 1፡25-27፣ … ይህም ቃል ከዘመናትና ከትውልዶች ተሰውሮ ምስጢር ሆኖ ቈይቶ ነበር፤ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል። [27] ለእነርሱም እግዚአብሔር የዚህ ምስጢር ክብር ባለጠግነት በአሕዛብ መካከል ምን ያህል እንደሆነ ለማሳወቅ መረጠ፤ እርሱም የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ ነው።

1) እነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች የሚያስረዱት እግዚአብሔር ሰውን ከውድቀት ለማዳንና በኃጢአት ምክንያት የጎደለውን ክብር ለመመለስ፣ የዘለዓለም ሕይወትም ለማውረስ ከአዳምና ከዋንት ትውልዶች ጀምሮ በነቢያቱ በኩል ሲሰዋ የቆየው የከበረው ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የገለጠበት ነው፡፡ ኤፌ 3፡3-6፣
2) ይኸኛውም ጥቅስ የሚያስረዳው የእግዚአብሔር ሕዝብ በሚባሉት እስራኤላዊያን ዘንድ ይናቁ የነበሩትና የሥራ ሕጉም ሆነ የተስፋ ቃሉ ያልተሰጣቸው፣ ከእግዚአብሔርም ጋር የቀረበ ህብረት ያልነበራቸው አህዛብ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ብቻ የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑበትና መዳን ያገኙበት መሆኑን የሚየያሳይ ነው፡፡ (ኤፌ 2፡11-22፣ ገላ 3፡26-29)

ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር ኅብረትና አንድነት/ የአንዱ እግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነትና ወደ አብ መቅረብ ያገኙበት የሰማያዊቱ አገር ኢየሩሳሌም ዜጋ የሆኑበት ነው፡፡

የከበረው እግዚአብሔር ለአብርሐም የሰጠው የበረከት ተስፋ አብረው ወራሽነት ያገኙበት፡፡ በክርስቶስ ሁሉም የሰው ዘሮች የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነትና ወደ አብ መድረስ ያገኙበት ነው፤

ጻድቁ እግዚአብሔር የአህዛብም አምላክ መሆኑና፣ ከየትኛውም ዘር የሆነ በኢየሱስ የሚያምነውን ህዝብ ሁሉ የሚያጸድቅ መሆኑን ያሳየበት ነው፡፡ በስራ፣ በዘር፣ መልካም ተግባር ለመፈጸም ምቹ ሁኔታ ላይ በመሆን ወይም አለመሆን ሳይሆን የጽድቅ ማግኛው መንገድ ሁሉም ሊያደርገው በሚችለው በእምነት፣ እንዲሆን ማድረጉን ያሳየበት ነው፡፡

3) ኤፌ 1፡9-10፣ በዘመን ፍጻሜ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ስር እንዲሆን/እንደሚገዛ ያቀደውን ዕቅድ የገለጠበት ነው፡፡ 1ቆሮ 15፡ 22-28፣ (ኤፌ 1፡21-23፣ ቆላ 1፡15-16)፡፡ ይህም በሚሆንበት ጊዜ በክርስቶስ የሆኑቱ የሚወርሱት ታላቅ ክብር ነው፡፡ ሮሜ 8፡17፤ ራዕ3፡21
በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሲፈጥር ቃል ብቻ በመናገር እንደነበርና፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሀው ላይ ሰፍፎ እንደነበር ሲገልጽ በመላው ብሉይ ኪዳን ስለ ኢየሱስ በግልጽ የሚናገረው ነገር አልነበረም፡፡ ያ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረበት ቃል፣ ኢየሱስ መሆኑና ፍጥረተ ዓለሙም ሁሉ የተፈጠረው በኢየሱስ ለራሱ ለኢየሱስ ክብር የመሆኑን ምስጢር ግልጽ የሆነበት ነው፡፡ ዮሐ ወንጌል 1፡1-3፣ ቆላ 1፡15-16፣

4) በአሁኑ ዘመን እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን አማካይነት የገለጠው ብዙ ገጽታ ያለው ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉ አለቆችና ስልጣናት እንዲታወቅ ያደረገበት ነው እንጂ ሞኝነት አይደለም፡፡ ኤፌ 3፡9-11፣

እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር በወንጌል አማካይነት የገለጣቸው ምስጢራት ሆነው ለዘመናት ቆይተው የነበሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

**መ. ብርሃን የእግዚአብሔር ፍጹም ትክክለኛነትን፤ የሁሉም ባህሪው እንከን አልባነትን (ፐርፌክሽን) የሚያመለክት ነው፡፡**

1ኛ ዮሐ 1፥5፣ "ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም የምንነግራችሁ መልእክት፣ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም፤ የሚል ነው።"

**ሠ. ብርሃን የጠራ መንፈሳዊ ዕውቀትን፣ ጥበብን፤ መረዳትን፣ የሚገልጥ ነው፤** (የዚህ ተቃራኒው፡- ማንኛውም የሃሰት መንፈሳዊ ትምህርትና፣ ሰው ሰራሽ ወጎች ናቸው)

2ቆሮ 4፡4፣6, የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል። 6 "በክርስቶስ ፊት እግዚአብሔር የክብሩን ዕውቀት ብርሃን ይሰጠን ዘንድ፣ "በጨለማ ብርሃን ይብራ" ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በልባችን አብርቶአልና።"

"ከሕፃንነትህም ጀምረህ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ዐውቀሃል።" 2ኛ ጢሞ 3፥15

ብርሃን በጭለማ የተሰወረውን ነገር እንዲታይ እንደሚያደርግ የወንጌሉ ቃልም መንፈሳዊ እውነትና የማይታየው እግዚአብሔር ጥበባዊ አሰራርና ምስጢራት እንዲታይ/እንዲታወቅ ያደርጋል፡፡

**ረ. ብርሃን የእግዚአብሔርን ክብር ያመለክታል፡-**

ራዕ 21፡23፣ "የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን ስለሚሰጣትና በጉም መብራቷ ስለ ሆነ፣ ከተማዋ ፀሓይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጋትም።" (ኢሳ 60፡19)

1ኛ ጢሞ 6፥16፣ "እርሱ ብቻ ኢመዋቲ ነው፤ ሊቀረብ በማይቻል ብርሃን ውስጥ ይኖራል፤ እርሱን ያየ ማንም የለም፤ ሊያየውም የሚችል የለም። ለእርሱ ክብርና ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን።" (የእግዚአብሔር ክብር ድምቀት እጅግ ታላቅና በስጋ ለባሽ ዓይን ሊታይ የማይቻል መሆኑን ያሳያል)

ወንጌል ብርሃን ነው ሲባል የመጀመሪያው ነገር ወንጌል የጠራ እውነት መሆኑን ያሳያል፡፡ አንድያ ልጁን ኢየሱስን ወደ ዓለም የላከው እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህን የአዲስ ኪዳን የምስራች ቃል መስበክ የጀመሩት እግዚአብሔር የላካቸው ቅዱሳን መላእክት ናቸው፡፡ በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላው መጥምቁ ዮሐንስም ይህንኑ አበሰረ፡፡ ጌታ ኢየሱስም

አብ እንደላከው የዓለም ብርሃን እውነትና መንገድ፣ ትሳኤና ህይወት፣ .... የዓለም አዳኝ መሆኑን አስተማረ፡፡ እግዚአብሔር አብም በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት አለ፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው ሐዋሪያትም ከወልድ የሰሙትና ያዩትን ከመንፈስ ቅዱስም የተማሩትን የወንጌል እውነት ሰበኩ፡፡ እኛም ይህን እውነት አምነን በመቀበል ዳንን/አተረፍን እንጂ አልከሰርንም/ሞኞች አይደለንም፡፡ ሰው ሞኝ የሚባለው/የሚሆነው ውሸትን አምኖ ሲታለልና ራሱ ባለቤቱን የሚያጠፋ ኃጢአት ሲያደርግ ነው፡፡ (ምሳሌ፡- አዳምና ሄዋን)

ስለዚህ ወንጌል እግዚአብሔር ከዘመናትና ከትውልድ ሁሉ ተሰውረው የነበሩ ምስጢሮች የገለጠበት ብርሃን ነው እንጂ ሞኝነት አይደለም፡፡ በእግዚአብሔርም ዘንድ ሞኝነት የለም/ደካማነትም የለም፡፡ እግዚአብሔር ሞኝ ሳይሆን ሁሉን አዋቂ ነው፣ ድክመት ያለበት ሳይሆን ደካሞችን የሚያበረታ ወሰን የሌለው ኃያል አምላክ ነው፡፡

አደርጋለሁ በማለት የተናገረውን መልካም ነገር በመፈጸም በተግባር የሚያሳይ፣ የእስራኤልን ሕዝብ በባርነት ይገዛቸው የነበረው የግብጹን ፈርዖንና ሰራዊቱን በኃያል ክንዱ ቀጥቅጦ ነጻ ያወጣ፣ ቀይ ባሕርን ከፍሎ ሕዝቡን በማሻገር አሳዳጆቻቸውን ያሰመጠ፣ ለ40 ዓመታት ሁሉ በምድረ-በዳ ይጓዙ የነበሩትን እስራኤላዊያን መና የመገበ፣ የኢያሪኮን ግንብ ያፈረሰ፣ በገባዖን ጸሐይና ጨረቃን ለአንድ ሙሉ ቀን ቀጥ አድርጎ ያቆመ፣ ሞቶ የተቀበረን ሰው በ4ኛው ቀን አስነስቶ በሕይወት እንዲኖር ያደረገ፣ በአጋንንት የታሰሩትን በብርቱ ክንዱ ነጻ እያወጣ ያለ፣ አሁንም ሕዝቡን በመንፈስ ቅዱስ እየሞላ ታይቶ በማይታወቅ ሰላምና ደስታ እየሞላ ያለ፣... ተቆጥረው የማያልቁ ተዓምራዊ ሥራዎች የሰራና እየሰራ ያለ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክን ያመነና የሚከተል ብርሃን በርቶለት፣ ዕውነትም ተገልጠጦለት ነው እንጂ በምንም ሚዛን ተሞኘ አያሰኝም፡፡

**የወንጌሉ ቃል ለተረዱት፡ -**

**የምስራች ቃል ነው**: - ሉቃስ 2፡10፣ 11፣ *መልአኩ ግን እንዲህ አላቸው፤ "አትፍሩ፤ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች አምጥቼላችኋለሁና። [11] ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀን ተወልዶላችኋልና፤ እርሱም ጌታ ክርስቶስ ነው።"* (በዚህ ጥቅስ፣ ወንጌል ቅዱሳን መላዕክት ሳይቀር የምስራች ዜና መሆኑን የመሰከሩለት ነው፡፡)

ከባርነት ነጻ መውጣትና ጸጋን መቀበያ ነው፡ - ዮሐ 10÷10፣ *"ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ ይመጣል፤ እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው መጥቻለሁ።"* (ይሄ ጥቅስ ደግሞ አምላክ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ለሰው ልጆች ከገዳዩ ዲያብሎስ ሊያድንና የተትረፈረፈ የዘላለም ሕይወት ሊሰጠን መምታቱን የተናገረው ወንጌል ነው፡፡

የእግዚአብሔር የክብሩ ዕውቀት ብርሃን የሚያበራ (የሚያስታውቅ) ቃል ነው፡፡ 2ቆሮ 4፡6

ሕይወት የሚሰጥ ቃል ነው፡ - “ስምዖን ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “ጌታ ሆይ፤ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤” ዮሐ 6፥68

የክርስቶስ ወንጌል በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኛ የነበረው የሰው ዘር ከራሱ ጋር የሚያስታርቅበት የእግዚአብሔር ጥበባዊ አሰራር ነው፤ 2ቆሮ 5፡19፣

የዓለምን ሕዝብ በክርስቶስ ኢየሱስ በፍቅር ወደ አንድነት የሚያመጣ፣ የአንድ ቤተሰብ አባል የሚያደርግ ቃል ነው፡፡ 1ቆሮ 12፡13፣ ገላ 3፡8

ይህን የወንጌል ቃል ሰምቶ በእምነት መቀበል ኃጢአት በሰው ሕይወት ላይ ከሚያስከትላቸው አደገኛ መዘዞች ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ወደ ህይወታችን የሚያመጣ ነው፡፡ ሮሜ 1፡16፣ “በወንጌል አላፍርም፤ ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤…” ሐሥ 11፡13-14፣

እግዚአብሔር የሰው ዘርን ምን ያህል እንደ ወደደና እርሱን ለመዋጀት ምን ያህል ታላቅ ዋጋ እንደ ከፈለ የሚያስተዋውቅ ቃል ነው፡፡ ዮሐ 3፡16

ሰይጣንን ድል በመንሳት የሰውን ዘር በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኛ መሆኑን እንዲያበቃ የሚያደርግ አዳኝ እንደ ሚመጣ የተስፋ ቃል የተሰጠው ጥንት ከአዳም ዘመን ጀምሮ ቢሆንም፣ ምንም ያህል ጊዜው ቢረዝምም እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል እንደ ሚፈጽም ታማኝነቱ ያረጋገጠበት ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ በምድር ስጋ ለብሶ ሲመላለስ እርሱ ለሰው ልጆች ኃጢአት ስርየት ለማስገኘት በራሱ ፈቃድ እንደ ሚሞትና ከሞትም እንደ ሚነሳ ተናግሮ የነበረውን በመፈጸም የሚሳነው ምንም ነገር እንደሌለ በተግባር ያሳየበት ጉልህ ማስረጃ ነው፡፡ ዮሐ 10፡18

ሰይጣን ግብረ-አበሮቹን አነሳስቶ ጌታ ኢየሱስን በማስገደል አስወግጄ የዚህ ዓለም ገዥነቴን አጸናለሁ ያለበትን የግድያ ጥበብ ቢጠቀምም፣ የወንጌሉ ቃል ባለቤት ጌታ ኢየሱስ ግን በእርሱ የሚያምን የሰው ዘርን ሁሉ የሚያድን የጽድቅ ሥራ በመሥራት ዲያብሎስንና ሞትን፣ አለቅነትን፣ የጨለማው ኃይላትና የሥልጣናትን ሁሉ በማያዳግም ሁኔታ (Irreversible) ድል አድርጎ ማዕረጋቸውን በመግፈፍ የእግዚአብሔር የሆኑትን ሁሉ ከጠላት እጅ ማርኮ ከሞት የተነሳበት አስደናቂ ጥበብ ነው፡፡ ኤፌ 4፡8-10፣ ቆላ 2፡14-15